*ረቡዕ፣ ጥቅምት ፳ ቀን፣ ፳፻፲፫ ዓመተ ምህረት*

**ግልጥ ደብዳቤ**

## ለውድ በአገር ቤትም በውጪም አገራትም ለምትኖሩ ኢትዮጵያዊያን
## ከአንድ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ፤ አንዱ ዓለም ተፈራ

# የኢትዮጵያ መንግሥት ሁሉን አቀፍ ድጋፍ ያስፈልገዋል!

አገራችን፤ አልለቅም ብሎ ከያዛት የተመሰቃቀለ የፖለቲካ አባዜ፤ በቀላሉ ልትወጣ አልቻለችም። ከዕለት ዕለት አዳዲስ ችግሮች እየተፈጠሩ፤ ከመሪም ሆነ ከተመሪ ትክክለኛ መንገድ ማፈላለጉ ጎድሎ፤ ከአዙሪት ወደ የኋሊት እየተንደረደርን፤ ወደፊት መሄዱ ቀርቶ፤ ባለንበት መቆም ተስኖናል። ይህ፤ በምንም መንገድ ልንሸፋፍነው የማንችል እውነት ነው። እስከመቼ ይሄን የኛ ሀቅ ብለን እንጓዛለን! እስከመቼ ኢትዮጵያዊነታችን በየጊዜው በሚመጣ አንዳንድ ጉዳይ ላይ ብቻ ያተኮረ ይሆናል!

ለኛ የግብጽ ጉዳይ፤ በዘመናት የሚቆጠር የቆላ ቁስላችን ነው። አገራችን ውስጥ ሰላም እንዳይኖር፣ አንድነት እንዳይኖር፣ ጠንካራ ኢትዮጵያ እንዳትኖር ያላደረጉት ነገር የለም። ዛሬም እንደትናንቱ ገፍተውበታል። አያስገርመንም። ግድባችን ላይ ጥቃት ሰነዘሩ አልሰነዘሩ፤ ውጤቱ እነሱኑ የሚለበልብ እሳት ይሆናል። የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድነት ያጠነክሩታል። ምላሹም በራሳቸው እጅ የሚጠመጥሙት፤ የራሳቸው ማነቂያ ገመድ ይሆናል። በውጪ ኃይሎች እጅ ያለውን ጉዳይ ወደ ጎድን ትተን፤ በጃችን ያለውን እውነታ እንመርምር። እስከዛሬ ድረስ፤ በግብፅ ማባበያ እየቋመጡ፤ አገራችንን ለመበታተን፤ ያገር ውስጥ አስተዳደሩና ደካማነት ተጨምሮበት፤ አሁን ኢትዮጵያ ካለችበት ሀቅ ደርሰናል። ለዚህ ሁሉ መሠረታዊ መፍትሔ እንዲሠጥ፤ ላንዴና ለመቼውም ሰላም፣ ዕድገትና ብልፅግና በአገራችን እንዲሰፍን፤ አስተዋፆ ማድረግ እንችላለን።

ባሁኑ ሰዓት፤ ከግብፅ፣ ከሱዳንና ከአሜሪካ ለተቃጣብን ጥቃት፤ የኢትዮጵያ መንግሥት አጣዳፊ ሙሉ አገራዊ ድጋፍ ያስፈልገዋል። ይህ ግን አንድ ጎድኑ ብቻ ነው። ሌላው ጎድኑ፤ ሁላችን ኢትዮጵያዊያን በአንድነት እንድንቆምና ለአገራችን ዘብ እንድንሆንላት፤ እንቅፋት የሆነውን የአንድነታችን ጠላት፤ የማስወገድ ግዴታ ነው። እኒህ አብረው የሚራመዱ ናቸው። አማራው በየቦታው እየተገደለና አገርህ አይደለም ተብሎ ሀብት ንብረቱ እየተቀማ፤ ለኢትዮጵያ ቁም ማለት አይቻልም። ሕገ-መንግሥቱ ኢትዮጵያዊ የምትሆነው በትግሬነትህ፣ በኦሮሞነትህ፣ በሶማሌነትህ እንጂ፤ በግለሰብ ኢትዮጵያዊነትህ አይታወቅም ብሎ ደንግጎ፤ ለኢትዮጵያ ቁም ማለት አይቻልም። በዚሁ ሕገ-መንግሥት፤ በትውልድ፣ በቋንቋ፣ በአስተዳደር የተከፋፈለ ክልልን አስቀምጦ፤ ለኢትዮጵያ ቁም ማለት አይቻልም። የተለያዩ ክልሎችን ይዞ፤ እኒህ ክልሎች የሚገናኙት ባለሥልጣኑ በፈቀደው መንገድና የአገሪቱን ጥቅም ለመከፋፈል የተሰባሰቡ በሆነበት ሀቅ፤ ለኢትዮጵያ ቁሙ ማለት አይቻልም።

እኛ በውጪ አገራት የምንኖር ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን፤ የተለያዩ የፖለቲካ እሳቤ ብንይዝም፤ ሁላችንንም የኢትዮጵያ ሕልውና፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነትና የአገሪቱ የወደፊት ዕድገት፤ ቀን ከሌት ያሳስበናል። ይህ ደግሞ፤ በሕዝቡ ኢትዮጵያዊነትና አንድነት እምነታችን ላይ የተመሠረተ ነው። ይህ በምድሩ ላይ ያለ ሀቅ ሲሆን ብቻ ነው እኛ እንቅልፍ የምናገኘው። የምናደርገው ማንኛውም አስተዋፆም አመርቂ ውጤት ይኖረዋል። ያለውን መንግሥት ስንደግፍ፤ መሠረትና ባለቤት የሆነው የሕዝቡ በአንድነት መቆም ወሳኝነቱን አምነን ነው። እናም የኢትዮጵያ መንግሥት፤ ይሄን ለሕዝቡ አንድነት ሆኖ መቆም እንቅፋት የሆነውን እንዲያስወግድ፤ መጠየቅ አለብን። ባለው ሕገ-መንግሥት የተማከለውና ሕዝቡን የከፋፈለው የክልል አስተዳደር ዋናው እንቅፋት ነው። እየተደረገ ያለው አማራን የማጥቃት ዘመቻው ትልቅ እንቅፋት ነው። የዚህ ሁሉ ጠንሳሽና አራጋቢ የሆነው መቀሌ የጎደበው ከፋፋይና በታኝ ቡድን፤ ለፍርድ አለመቅረቡ፤ ሌላው እንቅፋት ነው።

**ውድ በውጪ አገር የምትኖሩ ኢትዮጵያዊያን ሆይ!** እኛው ራሳችን በአንድነት ቆመን፤ በሥልጣን ላይ ያለውን መንግሥት በመደገፍ፤ ለወደፊቷ ኢትዮጵያ አስተማማኝ የሆነ ሕገ-መንግሥትና የአስተዳደር መዋቅር እንዲኖር ካልወተወትን፤ የያዘን አዟሪት መቸውንም አብሮን ይኖራል። ዴሞክራሲ ማለት ምርጫን በየተወሰነ ጊዜ ማካሄድ ማለት አይደለም። እንዴት ይካሄዳል? ማን ያካሂደዋል? እና ሌሎች አብረው መመለስ ያለባቸውን ጥያቄዎች ወደ ጎድን ትቶም የትም አይደረስም። ይህ ሁሉ ተደምሮ አንድ ገጹ ነው። ለምናደርገው ድጋፍ ሁሉ ውጤቱ ሊያረካን ይገባል። ግብፅ ግድባችንን መምታት ልትሞክር ወይንም ላትሞክር ትችላለች። እኛ፤ ኢትዮጵያዊነታችን ከግድቡ ጋር ብቻ የተያያዘ አይደለም። በርግጥ ግድቡ አንድ ገጽታ ነው። ዋናው አሳሪ ቁም ነገሩ፤ ኢትዮጵያዊያን በአንድነት ሆነን አብረን ወደፊት መመልከታችን ነው። ይህ ለዛሬና አሁን በጃቸው ላለው ብቻ ሳይሆን፤ ወደፊት ለሚመጡ ማናቸውም ችግሮች መፍትሔ ሠጪ ነው። ያ ነው ሊያረካን የሚገባው።

በዚህ ጉዳይ ለመመካከር ለምትሹ፤ በ eske.meche@yahoo.com ልታገኙኝ ትችላላችሁ።